የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፴ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No.66
ADDIS ABABA 5th September, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፬/፪ሺ፲፯
የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ……………………………………..……..ገጽ ፲፱ሺ፪፻፳

## Content

Proclamation No. 1394/2025
A Proclamation to amend the Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation…………..…...…Page 19220

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፬/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

**<u>የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

በምርጫ ጣቢያ እና በምርጫ ክልል ደረጃ የሚኖሩ ተግባራት አፈጻጸም ቀልጣፋ ለማድረግና የሚስተናገዱ ቅሬታዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሴቶችን፣ የአካል ጉዳተኞች እና የወጣቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማጎልበት እና ከዓለም አቀፍ የምርጫ መርሆች ጋር በማጣጣም ለመራጭነት እና ለዕጩነት የሚያበቃቸውን አሰራር መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥፋት ሲፈጽሙ ደረጃውን የጠበቀና እና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ሊታረሙ የሚችሉበትን እድል መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በምርጫ ሂደት ቴክኖሎጂን መጠቀም ወጭ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ፣ ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ያልተገቡ ድርጊቶችን ለመቀነስ የሚያስችል እና ተአማኒነት ያለው ምርጫ ለማካሄድ የሚረዳ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1394/2025

**<u>A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN ELECTORAL, POLITICAL PARTIES REGISTRATION AND ELECTION'S CODE OF CONDUCT PROCLAMATION</u>**

**WHEREAS** it is necessary to establish a system that ensure the efficiency of operations at the polling station and constituency levels and to effectively resolve complaints;

**WHEREAS** it is appropriate to create a system that qualifies women, persons with disabilities, and youth to vote and stand as candidates in order to enhance their political participation and to align with international electoral principles;

**WHEREAS** it is necessary to provide Political Parties with the opportunity to correct their wrongdoings in a fair and proportionate manner;

**WHEREAS** the implementation of technology helps to conduct cost effective, efficient, trustworthy election and reduce improper acts in election;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፬/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**ማሻሻያ**</u>

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፬) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፬) ተተክቷል፡-

"፳፬/ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማለት በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እና በምርጫ ክልል ደረጃ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡"

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡-

"፫/ ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከቱትን መሥፈርቶች፣ የጾታ ተዋጽኦ እና እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶችን ከግምት በማስገባት የምርጫ ክልል አስፈፃሚዎችን ይመለምላል ፣ ይመድባል፡፡ የምርጫ ክልል የሚኖረው የአስፈፃሚዎች ብዛት ምርጫ ክልሉ ያለውን የሥራ ጫና፣ የመራጮች ቁጥር፣ በምርጫ ክልሉ ሥር ያሉ የምርጫ ጣቢያዎችን ብዛት እና ሌሎች ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡"

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Article (1) of the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby Proclaimed as follows.

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as "The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct (Amendment) Proclamation No. 1394/2025.

2. <u>**Amendment**</u>

The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation No. 1162/2011 is hereby amended as follows:

**1**/ Article 2 Sub-Article (24) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (24):

"24/ Grievance Hearing Committee means a committee established in accordance with this Proclamation during elections to render administrative decisions on complaints lodged at a regional branch office and constituency level."

**2**. Article 13 Sub-Article (3) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (3):

"3/ The Board taking into consideration the criteria set out under Article 6 Sub-Article (1) of the Proclamation No. 1133/2019, gender representation, and other additional criteria, as appropriate, shall recruit and assign constituency election officials. The number of election officials in a constituency shall be determined by a Directive to be issued by the Board, taking into account the workload of the constituency, the number of voters, the number of polling stations under the constituency, and other factors."

፫. የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) ተተክቷል፡-

“፮/ እያንዳንዱ ምርጫ ክልል በምርጫ ክልሉ ኃላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሦስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ ሁለቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ከህዝብ የሚመረጡ ሲሆን ምርጫውም የጾታ ስብጥርን፣ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል አለመሆንን እና የመልካም ሥነ-ምግባር ምስክርነትን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡”

“፯/ የምርጫ አስፈጻሚ ወይም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ፣ ሥነምግባር ደንብ እና ሌሎች የዚህን አንቀጽ አፈጻጸም በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።”

፬. የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀፅ (፰) እና (፲) እንደሚከተለው ተስተካክሏል፡-

“፰/ ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፮ (፩) የተመለከቱትን መስፈርቶች፣ የጾታ ተዋጽኦ እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶችን በመጠቀም የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎችን ይመለምላል፤ ይመድባል። የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ብዛት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።”

“፲/ በዚህ አዋጅ መሰረት ለምርጫ ጣቢያ የሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ በምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ታይቶ ይወሰናል።”

፭. የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ለ) ተተክቷል፦

“፩/ (ለ) በድምጽ መስጫው ዕለት ዕድሜው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፤”

**3.** Article 13 Sub-Articles (6) and (7) of the Proclamation are repealed and replaced by the following new Sub-Articles (6) and (7):

“**6**/ Each Constituency shall have a three-member grievance hearing Committee Chaired by the Head of the Constituency. The two members of the Grievance Hearing Committee shall be elected from the public, and the selection shall take into consideration gender representation, non-membership of any political party, and evidence of good conduct.”

“7/ The Board shall issue a detail Directive regarding the selection of members of the election officials or grievance hearing committee, Code of Conduct, and other matters related to the implementation of this article.”

**4**. Sub-Articles (8) and (10) of Article 15 of the Proclamation are amended as follows:

“8/ The Board taking into consideration the criteria set out under Sub- Article (1) of Article 6 of Proclamation No. 1133/2019, gender representation, and other additional criteria as its necessary, shall recruit and assign poll workers. The number of poll workers shall be determined by a directive to be issued by the Board.”

“10/ Any complaint submitted to a polling station pursuant to this Proclamation shall be reviewed and decided by the head of the polling station.”

**5.** Article 18 Sub-Article (1) pharagraph (b) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (1) pharagraph (b):

“1/ (b) is 18 years old and above on the day of voting;”

፮. የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የመራጮች ምዝገባ ቦርዱ በሚወስነው የቴክኖሎጂ አማራጭ ሊከናወን ይችላል፡፡"

፯. የአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፯ ተተክቷል፡-

"፳፯/ <u>ምዝገባን ስለመቃወም</u>

ማንኛውም ሰው ወይም የእጩ ወኪል በመራጭ ምዝገባ ላይ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን ከነምክንያቱና ማስረጃው ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፶፫ (እንደተሸጋሸገ) መሰረት ይወስናል፡፡"

፰. የአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፡፡

"(፩/ (ለ) በድምጽ መስጫው ዕለት እድሜው ፳፩ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፤"

፱. ከአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

"፬/ የቀረበችው የግል እጩ ሴት የሆነች እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ ከ ፫ሺ (አንድ ሺህ) የማያንስ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይኖርባታል። ሆኖም የግል እጩ ተወዳዳሪዋ ሴት አካል ጉዳተኛ የሆነች እንደሆነ ማቅረብ ያለባት የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከ ፪ ሺ (ሁለት ሺህ) ያላነሰ መሆን ይኖርበታል።"

**6**. New Sub-Article (2) is added after Sub-Article (1) of Article 20 of the Proclamation. Hence, the existing Sub-Articles (2) and (3) of the Article are renumbered as Sub-Article (3) and (4), respectively.

"2/ Without prejudice to the prohibitions provided under Sub-Article (1) of this Article, the Board may decide voter registration to be conducted through technological alternatives."

7**.** Article 27 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 27**:**

**" 27/ <u>Objection to Registration</u>**

Any person or candidate's agent who has an objection to voter registration may submit a complaint, along with the reasons and evidence, to the head of the polling station. The head of the polling station shall decide in accordance with Article 153 (as renumbered) of this Proclamation."

**8.** Article 31 Sub-Article (1) pharagraph (b) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (1) pharagraph b:

"(1) b/ is 21 years of age or above on the date of voting;"

**9**. The following new Sub-Article (4) is added after Sub-Article (3) of Article 31 of the Proclamation. Hence, the existing Sub-Articles (4) and (5) of the Article are renumbered as Sub-Article (5) and (6), respectively:

"4/ If the independent candidate is a Woman, She shall submit a minimum of 3000 endorsement signatures that comply with the requirements stated under Sub-Article (1) of this article. However, if the woman independent candidate is a person with disability, the number of endorsement signatures required to be submitted shall not be less than 2000."

፲. ከአዋጁ አንቀጽ ፴፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ነባሮቹ ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፯) ያሉት ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፬)፣(፭)፣(፮)፣(፯) እና (፰) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

"፫/ የቀረበችው እጩ ሴት የሆነች እንደሆነ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምትወዳደር ከሆነች በምትወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሚኖሩ መራጮች አንድ ሺህ አምስት መቶ የድጋፍ ፊርማ፣ ሴት አካል ጉዳተኛ ከሆነች ፩ ሺ (አንድ ሺህ) የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይኖርባታል። የቀረበችው እጩ ለክልል ምክር ቤት እንደሆነ ፯፻፶ (ሰባት መቶ ሃምሳ) የድጋፍ ፊርማ፣ ሴት አካል ጉዳተኛ ከሆነች ደግሞ ፭፻ (አምስት መቶ) የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይኖርባታል።"

፲፩. የአዋጁ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፦

"፩/ (ለ) የመንግሥት ሰራተኛ በምርጫ ለመወዳደር እጩ ሆኖ ሲቀርብ የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄድበት ወቅት እና ምርጫው በሚከናወንበት ጊዜ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል።"

፲፪. ከአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፦

"፭/ ቦርዱ በምርጫ ለሚሳተፉ አካል ጉዳተኛ እና ሴት እጩ ተወዳዳሪዎች በተለይ ተፈጻሚ የሚሆን የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል፡፡"

፲፫. የአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፦

"፬/ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን የድምጽ መስጫው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡"

**10**. The following new Sub-Article (3) is added after sub-article (2) of Article 32 of the Proclamation. Hence, the existing sub-articles from sub-article (3) to (7) of the Article are renumbered as Sub-Article (4), (5), (6) (7) and (8), respectively:

"3/ If the candidate is a woman and is running for the House of People's Representatives, she shall submit 1500 endorsement signatures from the voters in the constituency for which she is running, and 1000 one (thousand) endorsement signatures if she is a woman with a disability. If the candidate is running for the Regional Council, she must submit 750(Seven Hundred Fifty) endorsement signatures and 500(Five Hundred) endorsement signatures if she is a woman with a disability."

**11.** Article 33 Sub-Article (1) phargraph (b) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (1) pharagraph (b) :

"1(b) A Civil servant contesting in an election as a candidate shall be granted leave with sallary during the campaign period and election time."

**12.** The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) of Article 44 of the Proclamation.

"5/ The Board shall issue a Directive on the use of mass media that are particularly applicable to candidates with disabilitie s and women participating in elections."

**13.** Article 54 Sub-Article (4) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (4):

"4/ The head of the Polling Station after assessing the complaints, notifies his decision in writing to the person or body lodging the complaints before the conclusion of voting."

**፲፬.** የአዋጁ አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፡-

"፮/ በድምፅ ቆጠራው ሂደት ግድፈት አለ በማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ቅሬታ ያቀረበ እንደሆነ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ጉዳዩን መርምሮ ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ ከ፲፪ (አስራ ሁለት) ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ወይም እንደ አግባብነቱ የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቀረበው አቤቱታ መሰረት የድምጽ ቆጠራው እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡"

**፲፭.** ከአዋጁ አንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯)፣ (፰)፣ (፱) እና (፲) ተጨምረዋል፡-

"፯/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ቦርድ አባል በማናቸውም ሁኔታ ስራውን በለቀቀ ፩ (አንድ ዓመት) ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም አመራር መሆን፣ ወይም በ ፴ (ሦስት) ዓመት ጊዜ ውስጥ የግል እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም፡፡"

"፰/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመራርነት ቦታ ላይ ያለ የቦርዱ ሠራተኞች በማናቸውም ሁኔታ ሥራውን በለቀቀ በ፪ (ሁለት ዓመት) ጊዜ ውስጥ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም አመራር መሆን አይችሉም፡፡"

"፱/ በፍርድ ቤት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርድ ውሳኔ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት የታገደ ሰው የዕግዱ ጊዜ እስኪያበቃ የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችልም።"

**14.** Article 58 Sub-Article (6) of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Sub-Article (6):

"6/ If a Political party or an agent of an independent candidate submits a complaint alleging flawed counting process, the head of the Polling Station has to investigate and decide on the complaint immediately or no later than 12 (Twelve Hours).The head of the Polling Station or, as appropriate, the constituency grievance hearing committee may decide the vote counting process to be discontinued or stopped and as its necessary, a re-count to be conducted based on the complaint."

**15.** The following new Sub-Article (7), (8), (9) and (10) are added after SubArticle (6) of Article 63 of the Proclamation:

"7/ Subject to the provisions of Sub-Article (4) of this Article, members of the Management Board may not, under any circumstances, become members or leaders of any political party within five years, or become an independent candidate within three years of leaving office."

"8/ Subject to the provisions of Sub-Article (4) of this article, employee of the Board in leadership position may not, under any circumstances, become member or leader of any Political Party within two years of leaving office."

"9/ A person who has been banned from political party membership by a judicial decision or by a Board decision pursuant to this Proclamation shall not become a member of any political party for the duration of his ban."

"፲/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) እና (፰) የተደነገገውን የጣሰ የቀድሞ የሥራ አመራር ቦርድ አባል ወይም በአመራርነት ቦታ ላይ ያሉ የቦርድ ሠራተኞች ከፖለቲካ ፓርቲው አባልነት እንዲሰረዝ ቦርዱ ይወስናል።"

**፲፮.** የአዋጁ አንቀጽ ፷፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) ተሽረው በሚከተሉት አዲስ ፊደልተራ (ሐ) እና (መ) ተተክተዋል፡-

"ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ(ለ) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀሪዎቹ መሥራች አባላት መደበኛ ነዋሪነታቸው የሌሎች ቢያንስ ፮ (ስድስት) ክልሎች ሲሆኑ፤" እና

"መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት ከስድስቱ ክልሎች ለሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ መሥራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በእያንዳንዱ ክልል ቢያንስ አሥር በመቶው መደበኛ ነዋሪ ሲሆኑ ነው፡፡"

**፲፯.** የአዋጁ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ተሽሮ በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ተተክተዋል፡-

"፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመስራች ጠቅላላ ጉባኤውን ካካሄደ በኋላ የምዝገባ ማመልከቻው በፖለቲካ ፓርቲው መሪ ተፈርሞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት፡፡"

"፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩት ሰነዶች ዋና እና የኤሌክትሮኒክ ቅጂ ከምዝገባ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡"

"10/ The board shall decide to revoke Political Party membership of a former Management Board member or employee of the Board in leadership position who violates provision of Sub-Article (7) and (8) of this Article."

**16.** Article 64 Sub-Article (1) pharagraph (c) and (d) of the Proclamation are repealed and replaced by new Sub-Article 1 pharagraph (c) and (d):

" (c) Subject to Sub-Article (1)pharagraph (b) of this Article, the remaining founding members are permanent residents of at least six other regions, and"

"(d) The number of members registered as founders from the six regions as laid down in Sub-Article (1) (c) of this article, shall constitute at least ten percent (10%) of the total founding members from each regions."

**17.** Article 67 Sub-Article (1) and (3) of the Proclamation are repealed and replaced by new Sub-Article (1) and (3):

"**1**/ Any political party, after conducting its founding general assembly shall submit a registration application signed by its leader."

"**3**/ The Original and Electronics copies of the documents listed under Sub-Article (2) of this Article shall be submitted with the registration application."

፲፰. የአዋጁ ምዕራፍ ሰባት ርዕስ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ርዕስ ተተክቷል፡-

**"ምዕራፍ ሰባት**
**የፖለቲካ ፓርቲ መታገድ፣ መሰረዝ ወይም መፍረስ"**

፲፱. ከአዋጁ አንቀጽ ፺፮ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፯ ተጨምሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ከአንቀጽ ፺፯ እስከ ፩፻፶፱ ያሉት ነባር አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፺፰-፩፻፷ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

**"፺፯/ የፖለቲካ ፓርቲ መታገድ**

"(፩) ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፱ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) (ሰ)፣ (ሸ)፣ (በ) ወይም (ተ) በተመለከተው አግባብ ጥሰት መፈፀሙ የተረጋገጠ የፖለቲካ ፓርቲን የጥሰቱን አይነት፣ ክብደት እና ሌሎች ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል።"

"(፪) ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በፖለቲካ ፓርቲ ላይ የእገዳ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ፓርቲው መከላከያውን አቅርቦ እንዲሰማ ማድረግ አለበት።"

"(፫) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የታገደ የፖለቲካ ፓርቲ እገዳው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ማንኛውንም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ በየትኛውም ደረጃ በሚደረግ ምርጫ ላይ መሳተፍ እና በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ መሳተፍ አይችልም፤ ከመንግስት የሚገኝ ድጋፍ ተጠቃሚ አይሆንም።"

"(፬) የእግድ ውሳኔ የተላለፈበት የፖለቲካ ፓርቲ ሌላ ጥፋት ከፈፀመ ቦርዱ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌን መከተል ሳይጠበቅበት ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።"

"(፭) ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ያሳለፈውን የእገዳ ውሳኔ የሚቃወም የፖለቲካ ፓርቲ የቦርዱ ውሳኔ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።"

18. The Title of Chapter Seven of the Proclamation is repealed and replaced by the following New Title:

**"CHAPTER SEVEN**
**SUSPENSION, DE-REGISTRATION OR DISSOLUTION OF POLITICAL PARTY"**

19. The following new Article 97 is added after Article 96 of the Proclamation. Hence, the existing Articles from 97 to 159 of the Proclamation are renumbered as Articles 98 to 160, respectively:

" **97/ Suspension of a Political Party**

1/ The Board may decide to suspend a political party found to have violated the provisions of Article 99 (as renumbered) sub-article (1) a, b, g, h, j and k of this Proclamation for a period not exceeding five years having regard to the nature, severity and other circumstances of the violation. "

"2/ The Board, before deciding to suspend a political party as per Sub-Article (1) of this Article, shall give the party an opportunity to present its defense and be heard."

"3/ A political party suspended as per Sub-Article (1) of this Article is, during the period of the suspension, prohibited from any Political activity, from participating in elections at any level, and participating in the Joint Council of Political Parrties; and shall not benefit from grants provided by the government."

"4/ Where a political party that has been suspended for a previous offense commits another offense, the Board shall take appropriate legal measure without complyning the provision of Sub-Article (2) of this Article."

"5/ A Political Party that objects to a suspension decision made by the Board pursuant to this Article may lodge an appeal to the Federal High Court within 30 days of receipt of the decision."

፳. ከአዋጁ አንቀጽ ፺፱ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ረ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ሰ)፣(ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ) እና (ተ) ተጨምረዋል፡-

"(ሰ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተቀመጠው ዝቅተኛ የፖለቲካ ፓርቲ መሥራች አባላት ቁጥር የተጓደለ እንደሆነና ፓርቲው ይህንኑ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል በቦርዱ ተገልፆለት ሳያስተካክል የቀረ እንደሆነ፤"

"(ሸ) አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት በሚያቀርበው የሒሳብ ኦዲት ሪፖርት ላይ ጉልህ የሆነ የሒሳብ ጉድለት ወይም ምዝበራ ስለመፈጸሙ ከተረጋገጠ፤"

"(ቀ) በግለሰቦች፣ በብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መካከል ፣ ግጭትን፣ ጥቃትን እና ጥላቻን የሚፈጥር ድርጊት የፈፀመ እና እንደጉዳዩ ክብደት እየታየ ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከድርጊቱ ያልተቆጠበ ወይም ማስተካከያ ያላደረገ እንደሆነ፤"

"(በ) አባላትን ከፍላጎታቸው ውጪ በኃይል ወይም በማስገደድ የመለመለ እና እንደጉዳዩ ክብደት እየታየ ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከድርጊቱ ያልተቆጠበ እንደሆነ፤"

"(ተ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን ሕጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ እና እንደጉዳዩ ክብደት እየታየ ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከድርጊቱ ያልተቆጠበ ወይም ማስተካከያ ያላደረገ እንደሆነ፤"

**20.** The following new Sub-Article (g),(h),(i),(j) and (k) are added after Sub-Article (1) pharagraph (f) of Article 99 (as renumbered) of the Proclamation:

"(g) If the minimu**m** number of founding members of a political party provided by this Proclamation has been goes down from the minimum number and the party does not rectify the situation within two months of being notified to do so by the Board; "

" (h) Without prejudice to prosecution by the relevant criminal law, where the audit report submitted in accordance with Sub-Article (1) pharagraph (b) of this Article confirms that a significant financial deficit or embezzlement has been committed by the Political Party; "

" (i) If the party has committed acts that cause conflict, violence and hatred among individuals, nations, nationalities and peoples and has not refrained from such acts or made corrections within a time limit set by the Board, taking into account the gravity of the matter; "

" (j) If the party has recruited members against their will by force or coercion and has not refrained from such act or made corrections within a time limit set by the Board, taking into account the gravity of the matter; "

" (k) If the party has obstructed the lawful and peaceful political activities of another Political Party and has not refrained from such act or made corrections within a time limit set by the Board, taking into account the gravity of the matter;"

፳፩. ከአዋጁ አንቀጽ ፩፻፩ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨምሯል፡-

“፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው ቢኖርም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተመለከተውን የአባላት መዋጮ ቢያንስ (፳) ሃያ በመቶ ከሆኑት አባላት መሰብሰቡ ካልተረጋገጠ በቀር ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ አያገኝም፡፡”

፳፪. ከአዋጁ አንቀጽ ፩፻፱ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡-

“፭/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመንግስት መስሪያ ቤትን ወይም በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅትን የፋይናንስ እና የክፍያ ስርዓትን አሰራር በመጠቀም ከመንግስት ወይም ከልማት ድርጅት ሰራተኛው ደሞዝ፣ አበል ወይም ከማንኛውም አይነት ክፍያ ላይ የአባልነት መዋጮ ወይም ሌላ ማንኛውንም አይነት የገንዘብ ድጋፍ መቀነስ ወይም መሰብሰብ አይችልም።”

፳፫. የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፳፫ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

“፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ወኪሉ ያልተገኘው ሆን ተብሎ በተቀነባበረ መሰናክል ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወኪሉ ሳይኖር የተከናወኑ የምርጫ ተግባራት እንዲሰረዝለት ወኪሉ እንደአግባብነቱ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት መጠየቅ ይችላል።”

21. The following new Sub-Article (6) is added after Sub-Article (5) of Article 101 (as renumbered) of the Proclamation:

“6/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) pharagraph (b) of this Article, a political party shall not receive financial support from the government unless it is proven that the party has collected membership contribution specified in it’s by laws from at least 20% percent of its members.”

**22.** The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) of Article 109 (as renumbered) of the Proclamation:

“5/ Any Political Party may not deduct or collect membership contribution or any other financial support from the salary, allowance or any other payment of a civil servant or an employee of a public enterprise by utilizing the financial and payment system of a government office or a public enterprise.”

**23.** Article 123 Sub-Article (2) (as renumbered) of the Proclamation is repeale d and replaced by a new Sub-Article (2):

“2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, where it is established that the agent’s absence was a result of an obstacle deliberately designed to hinder his presence, the agent may request, as appropriate, the activities conducted in his absence to be annulled by the constituency grievance hearing committee or the head of the polling station.”

**፳፬.** በአዋጁ አንቀጽ ፩፻፶፫ (እንደተሸጋሸገ) ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮)፣ አንቀጽ ፩፻፶፭ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ (፩) እና (፪)፣ እና አንቀጽ ፩፻፶፮(እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደሚከተለው ተሰተካክሏል፦

"አቤቱታ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቀርባል በሚል የተደነገገው ቅሬታው ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ይቀርባል በሚል ተተክቷል።"

**፳፭.** ከ አዋጁ አንቀጽ ፩፻፷ (እንደተሸጋሸገ) ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ ፩፻፷፩ ተጨምሯል፡፡ በዚሁም መሰረት ከአንቀጽ ፩፻፷ እስከ ፩፻፷፬ ያሉት ነባር አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፻፷፪፣ ፻፷፫፣ ፻፷፬፣ ፻፷፭ እና ፻፷፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"፩፻፷፩. <u>ቴክኖሎጂ እና ብሔራዊ መታወቂያ ስለመጠቀም</u>

"፩/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ለእጩነት የሚያበቁ የመመዘኛ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የእጩ ምዝገባ ፣ የእጩዎች ድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ ወይም ማረጋገጥ፣ መራጮች ምዝገባ፣ የድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራ፣ ውጤት ማረጋገጥ ሂደት ወይም ሌሎች የቦርዱን ስራ ውጤታማ ሊያደርግ በሚችሉ ተግባራት ላይ ቴክኖሎጂን ሊጠቀም ይችላል።"

"፪/ ማንኛውም ሰው በዕጩነት ለመመዝገብ የብሔራዊ መታወቂያ ሊኖረው ይገባል።"

"፫/ ማንኛውም ሰው የፖለቲካ ፓርቲን በመስራችነትም ሆነ በአባልነት ሲቀላቀል፣ ለእጩ የድጋፍ ፊርማ ሲሰጥ እና ቦርዱ በሚወስናቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ሲወስን የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ሊኖረው ይገባል።"

**24.** The Phrase of Sub-Article (1) to (6) of Article 153 (as renumbered), Sub-Article (1) and (2) of Article 155 (as renumbered) and Sub-Article (1) of Article156 (as renumbered) is ammended as follows:

"The provision that the complaint shall be submitted to the polling station's grievance hearing committee has been replaced with the provision that the complaint shall be submitted to the polling station head."

**25.** The following new Article 161 is added after Article 160 (as renumbered) of the Proclamation. Hence, the existing Articles 160 to 164 are renumbered Article162, 163,164,165and 166, respectively.

**"161/ <u>The Use of Technology and National Identity Card</u>**

"1/ The Board may use technology in the registration of candidates who meet the eligibility criteria set forth in this Proclamation, collection or verification of endorsement signature of candidates, voter registration, voting, counting, verification of results, and other activities that may enhance the efficiency of the Board's work."

"2/ Any person applying for candidate registration needs to have National Identity Card."

"3/ Any person seeking to join a Political Party as a founder or a member endorses a canidadate and on other cases where the Board decides shall produce National Identity Card."

"፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ን በተመለከተ የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎች ቦርዱ የተለየ የማንነት ማረጋገጫ ማቅረብ የሚቻልበትን ወይም የዚህን አንቀፅ አፈፃፀም በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡"

፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፴ ቀን 2017 ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

"4/ The Board shall issue a Directive regarding the provision of alternative proof of identity in areas where the national identity card is not accessible, or the implementation of this Article, with regard to Sub-Articles (1) and (3) of this Article."

3. **Effective date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its approval by the House of People's Representatives.

**Done at Addis Ababa, on this this day of 5th September, 2025**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**